# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 357 መጋቢት 5 2007 ገጽ 1


አርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሕዝባዊ እምቢተኝነትንና ሕዝባዊ አመጽን አቀናጅቶ ለመምራት የተዘጋጀ፤ ለዚህ የሚያበቃው ድርጅታዊ አቅም እየገነባ ያለ ድርጅት ነው። አርበኞች ግንቦት 7 “እንሰባሰብ በወያኔ ላይ የምናቀርባቸው ተቃውሞዎች በሙሉ ወደ እምቢተኝነት ከፍ እናድርጋቸው” ይላል።

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ ወጣቶችንና ህፃናትን እያፈሰ ወደ ውትድርና ካምፖች እያጋዘ መሆኑ ታወቀ

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ፋሺስታውን አገዛዝ እየከዱ የሚሰወሩና ለህዝብ ወገንተኝነታቸውን በማሳየት የነፃነት ትግሉን የሚቀላቀሉ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱም ታውቋል።

ከመከላከያ ሰራዊቱ የሚከዱ አባላት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱን ተከትሎ ከፍተኛ ወጥረት ውስጥ የሚገኘው የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በግዳጅ ወጣቶችንና እድሜያቸው ለውትድርና ያልደረሱ ህፃናትን በማፈስ ወደ ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፖች እያጋዘ እንደሚገኝ ምንጮቻችን ጠቆሙ። ባሳለፍነው ሳምንት በሐረር ከተማ እንደ አዲስ በተጀመረው አፈሳ በርካታ በቀን ስራ የሚተዳዳሩ ነዋሪዎች ታፍሰው ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛዎች ተወስደዋል። በአፈሳው እድሜያቸው ከ12 እስከ 13 አመት የሚደርሱ ወጣቶችም ወደ ማሰልጠኛ የተወሰዱ ሲሆን፣ ወላጆች የትውልድ ዘመን ማስረጃ ሰርቲፊኬት ይዘው ልጆቻቸውን ለመታደግ ቢሄዱም፣ መልስ ባለማግኘታቸው፤ እናቶች በልጆቻቸው መሄድ ሲያልቀሱ እንደነበር የአይን እማኞች ለሬዲዮ ክፍላችን ያደረሱን መረጃ ያመለክታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጥቂት የማይባሉ ወጣቶቹ በመከላከያ ውስጥ የተሻለ ትምህርትና የውጭ እድል ይሰጣችኋል በሚል ሽንገላ ተታለው መመዝገባቸውን ለማወቅ ችለናል። አፈሳው በአፋር ክልልም በተመሳሳይ መልኩ እየተፈጸመ እንደሚገኝ ታውቋል።

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝን የሚከዱ የሰራዊት አባላትን ለመተካት፤ እና እየተመናመነ የመጣውን የመከላከያ ሰራዊት ለማጠናከር በሚል በተለያዩ ጊዜያት አዲስ አባላትን ለመመልመል አገዛዙ ማስታወቂያዎችን ቢያወጣም ተመዝጋቢ ማጣቱን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ ለነባርና ተቀናሽ የሰራዊት አባላት ዳግም የተቀላቀሉን ጥሪ ማቅረባቸው አይዘነጋም። ይሁን እንጅ ተቀናሽ የሰራዊት አባላት ለቀረበላቸው ጥሪ ምላሽ አለመስጠታቸው የተዘገበ ሲሆን የተለያዩ መሸንገያ እና ማባበያ በአገዛዙ ቢቀርብላችም አሻፈረኝ ማለታቸው ይታወሳል።

## አዲስ አበባ ኮልፌ ቀራንዮ ዉስጥ ክፍለ ከተማ የወያኔዉ ቅጥረኛ ከፍተኛ ድብደባ ደረሰበት

ከድብደባው በኋላ የህዝብ እንባ በከንቱ አልቀረም ሲሉ የአካባቢው ነዋሪዎች ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ በወረዳ 1 ውስጥ የጉጅሌው ወያኔ ቅጥረኛ የሆነውና የወረዳውን ህዝብ ሲያሰቃይና ሲያስለቅስ የነበረው የደንብ ማስከበር ሃላፊ ኮማንደር ግደይ የተባለ ጭፍራ ትላንት የካቲት 27 / 2007 አ.ም የነዋሪዎችን መኖሪያ ቤት በሐይል ለማፍረስ በሄደበት ቦታ በገጀራ ተቆራርጦ መጣሉ ታወቀ። ግለሰቡ በአሁኑ ሰአት በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ክትትል እየተደረገለት ቢሆንም የመዳን ተሳፋው የተመናመነ መሆኑ ታውቋል።

የጉጅሌው ጭፍራ ግደይ በተለይ ዘነበወርቅ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ባነስተኝ ንግድ የሚንቀሳቀሱ ነዋሪዎችን የንግድ ቦታዎቻቸውን ያለምንም ከልካይ በማሸግ፤ የግል ንብረቶቻቸውን እያወጣ በማናለብኝነት በእሳት ሲያቃጥል የነበረ መሆኑን ለማወቅ ችለናል። የነዋሪዎች እርምጃ በተለይ ለፋሽስታዊው አገዛዝ በቅጥረኝነት እያገለገሉ በህዝብ ላይ ከፍተኛ በደል ለሚፈጽሙ አረመኔ ካድሬዎች የማስጠንቀቂያ ደዎል ሲሆን እንደሚችል በስፋት እየተነገረ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ ዜና በፋሽስቱ ወያኔ የጥፋት ክንፍ በሆኑት በብአዴን እና በኦህዴድ ሹማምንት መካከል የተፈጠረው ሽኩቻ ተባብሶ መቀጠሉ ተሰማ። የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ እየተፈረካከሰ ባለበት በዚህ ወቅት በሁለቱ ክንፎች የነገሰው ሽኩቻና አለመተማመን በድርጅቱ ህልወና ላይ ከፍተኛ አደጋ መደቀኑ ተነግሯል። አንዳንድ የድርጅቶቹ ቱባ ሹማምንት .... ( ወደ ገጽ 3 ዞሯል )

ግዜ

## በየቦታዉ በመፋፋም ላይ ያለዉ ህዝባዊ ተቃዉሞ ወያኔ ካምፕ ውስጥ ከፍተኛ ፍርሃትና ድንጋጤ ፈጠረ

ከህዝባዊ ተቃውሞች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ፍርሃት ውስጥ የሚገኘው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ህዝባዊ ስብሰባዎችና ሰልፎች እንዳይካሄዱ አፋኝ ህጎችን ቢዘረጋም ጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በፋሽስታዊው አገዛዝ ላይ ያለውን ተቃውሞ በተለያዩ መንገዶች መግለጹን አጠናክሮ መቀጠሉ ታውቋል። በተለይ በአዲስ አበባ እና በአንዳንድ የክልል ዋና ከተሞች በተለያዩ ስፍራዎች የሚገኙ ግድግዳዎችና የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች በየእለቱ “ጭቆና በቃን! ነጻነትና ፍትህ እንፈልጋለን! ለነጻነት ትግል ተነስ!” በሚሉ መፈክሮች አሸብርቀው መታየታቸው የተለመደ ክስተት መሆኑ ለፍርሃቱ መንገስ አብይ ምክንያት መሆናቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን እየተካሄዱ ያሉት ህዝባዊ ተቃውሞች የኢትዮጵያ ህዝብ ፋሽስታዊውን አገዛዝ አንቅሮ ለመትፋቱ ማረጋገጫ ሊሆኑ እንደሚችሉ በስፋት እየተነገረ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። በቅርቡ ደግሞ እነኚሁ የፍትህና የነጻነት ጥያቄዎች በመገበያያ የብር ኖቶች ላይ ሳይቀር እየተፃፉ በስፋት እየተስተዋሉ መሆናቸው ከአገር ቤት የደረሱን መረጃዎች ያመለክታሉ። ሂደቱ በዚህ ከቀጠሉ የብር ኖቶች በሙሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ በህዝባዊ ጥያቄዎችና የተቃውሞ በመፈክር ጽሁፎች መጥለቅለቃቸው እንደማይቀርም ምንጮቻችን ተናግረዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ በቦሌ አካባቢ የሚገኙ ግድግዳዎችና አጥሮች ”መሪዎቻችን ይፈቱ! ፍትህ ለኮሚቴዎቻችን! ጭቆናው ይብቃ!” በሚሉ የህዝበ ሙስሊሙን ጥያቄዎች በሚያስተጋቡና በሌሎች መሰል መፈክሮች ተሞልተው መታየታቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

## በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ የነገሰው አለመተማመን ተባብሶ መቀጠሉ ተሰማ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሰራዊት አባላት እና ከፍተኛ መኮንኖች ላይ ዘርን ያማከለ ቅነሳ ለማድረግ ዝግጅት ማጠናቀቁን ምንጮቻችን አመልክተዋል።

በመከላከያ ሰራዊቱ የተለያዩ እዞች ውስጥ በተንሰራፋው ዘረኝነትና ፍጹም አምባገነናዊ አስተዳደር የተነሳው የነገሰው አለመተማመን ተባብሶ መቀጠሉን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የሰራዊቱ አባላት የሆኑና በአመራርነት በማገልገል ላይ የሚገኙ የአማራ እና ኦሮሞ ብሄር ተወላጆችን ለመቀነስ ዝግጅት ማጠናቀቁን ለማወቅ ተችሏል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ፋሽስታዊው አገዛዝ ሁለቱ ብሄሮች ላይ ብቻ ያነጣጠረ የጥቃት ዘመቻ ለማድረግ መወጠኑ በተለይ በሰራዊቱ ውስጥ ለሚነሱ ማንኛውም የመብት ጥያቄዎች አንቀሳቃሽ ሞተሮች ናቸው በሚል እንደሆነ ታውቋል። አገዛዙ ጥቂት የማይባሉ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ የመብት ጥያቄዎችን በማንሳት የእዝ ሹማምንትን ይሞግቱ ለነበሩ እና ተሰርቶ በተጠናቀቀው ብሄር ተኮር ቅነሳ ላይ ስማቸው የሰፈረ የሰራዊት አባላትና መኮንኖችን ከቅነሳ በኋላም ከፍተኛ ስጋት ሊፈጥሩ ይችላሉ በሚል ስጋት በወንጀል ለማጥመድና ለማሰር ሴራዎችን በመጎንጎን ላይ መሆኑንም ምንጮቻችን አመልክተዋል።

በተያያዘ ዜና በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ የነገሰውን የለውጥ ጥያቄ ያነሱ የሰራዊት አባላትና መኮንኖች ከተለያዩ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች እንዲሁም በሀገር ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ጋር በመተባበር የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝን ህልው አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ የሚል ስጋት በወያኔ መንደር በአዲስ መልክ ማገርሸቱን ለማወቅ ተችሏል። በተለይ የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ በሁሉም ረገድ በእጅጉ እየጠናከረ መሄድ በወያኔ መንደር ለተቀሰቀሰው ስጋት መንስኤ መሆኑ ታውቋል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ ስራ እያከናወነ እንደሚገኝ መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን በሰራዊቱ ውስጥ የሚገኙት የአርበኞች ግንቦት 7 ሰዎች የውስጥ አርበኝነት ስራቸውን በአግባቡ እየከወኑ መቀጠላቸውን ለሬዲዮ ክፍላችን የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

## በህወሓት ላይ የሚቀርቡ ተቃውሞዎች ሁሉ ወደ እምቢተኝነት ይደጉ !

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአለፉት 23 ዓመታት በህወሓት ዘረኛ አገዛዝ የደረሰበት ስቃይ እንዲቀንስ፤ ገዢዎቹ ከጫንቃው እንዲወዱ፤ ህወሓትን አውርዶ የሚፈልጋቸው መሪዎችን በነፃነት እንዲመርጥ ሲጠይቅና አቤቱታ ሲያሰማ ቆይቷል። በ1997 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝብ ምኞት የሚሳካ መስሎ የታየ የነበረ ቢሆንም በአገዛዙ አረመኔዓዊ እርምጃ ተሰናክሏል። ከጥቂት ዓመታት ወዲህ "ድምፃችን ይሰማ" የሚሉ አቤታዎች ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መምጣት ጀምሯል – "ድምፃችን ይሰማ ሙስሊሞች"፣ "ድምፃችን ይሰማ አርቶዶክሶች"፣ "ድምፃችን ይሰማ መምህራን"፣ "ድምፃችን ይሰማ ተማሪዎች"፣ … ወዘተ። በተለይ ሙስሊም ወገኖቻችን በተደራጀ መንገድ "ድምፃችን ይሰማ" እያሉ ሲወተውቱ ሦስት ተከታታይ ዓመታት አልፈዋል። ወገኖቻችን "ድምፃችን ይሰማ" በማለታቸው ተደብድበዋል፣ ታስረዋል፣ ተገድለዋል።

አቤቱታ የሚሰማ ጆሮ የሌለው አገዛዝ ሲገጥም ምን ይደረጋል? ለአቤቱታ አቅራቢው ያለው ምርጫ ከሁለት አንድ ነው። ወይ አቤቱታን እርግፍ አድርጎ ጥሎ በደልን ተቀብሎ "እህህ !" እያሉ መኖር፤ አሊያም "በቃኝ፣ እንቢ አልገዛም" ማለት፤ ሦስተኛ ምርጫ የለም።

አቤቱታ ሰሚ ሲያጣ እና ሕዝብ መሮት "እንቢኝ፣ አልገዛም" ሲል ነው ሕዝባዊ እምቢተኝነት ተቀሰቀሰ የሚባለው። ሕዝባዊ እምቢተኝነት ብዙ መልኮችና ቅርጾች ቢኖሩትም ዋነኛዎቹ መገለጫዎች ሁለት ናቸው። አገዛዙ ሕዝብ እንዲያደርግ የሚፈልገውን አለማድረግ እና/ወይም አገዛዙ ሕዝብ እንዲያደርግ የማይፈልገውን ማድረግ።

ለምሳሌ፣ አገዛዙ ሹማምንቱ እንዲከበሩ፣ ሕዝብ እንዲታዘዝላቸው ይፈልጋል፤ እንቢ ያለ ሕዝብ ግን የአገዛዙን ሹማምንት ይንቃል፣ በየደረሱት ያዋርዳቸዋል፣ "አልታዘዛችሁም" ይላቸዋል። ማንኛውም መንግስት የዳኝነት ሥርዓቱ እንዲከበርለት ይፈልጋል፤ በደል የመረረው ሕዝብ ግን የአምባገነኖች ችሎት ውሳኔ አይቀበልም፤ ዳኞችንም ዳኝነትንም አያከብርም። ሕዝብ የመንግሥትን ግብር በወቅቱ እንዲከፍል የማንኛውም መንግሥት ፍላጎት ነው። በመንግሥት ያመረረ ሕዝብ ግን ግብር አይከፍልም፤ መክፈል ግድ ከሆነበትም አዘግይቶ፣ አስለፍቶ ነው። የመረረው ሕዝብ ምሬቱን መፃፍ በሌለበት ቦታ ይጽፋል። በደል የበዛበት ሕዝብ "ዝም በል" ሲሉት ይናገራል፤ "ተናገር" ሲሉት ዝም ይላል።

አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ የሕዝባዊ እምቢተኝተኝነት እርምጃዎች ጅምሮች እየታዩ ነው። በአማራ ክልል፣ ሕዝብ በሹማምንት ላይ የራሱን እርምጃ መውሰድ ጀምሯል። ሕዝብ ራሱ የፓሊስንም የፍርድ ቤትንም ሥራ ተክቶ እየሠራ ነው። ይህ መበረታታት ያለበት ትልቅ እርምጃ ነው። እንደዚሁም ሁሉ በተለይ ወጣቶች ብሶቶቻቸውን በብር ኖቶች ላይ ጽፈው ገበያው እንዲያዘዋውራቸው እያደረጉ ነው። ይህም "የወረቀት ገንዘብን ለተሠራበት ዓላማ ብቻ ተጠቀሙ" የሚለውን ህግ በመጣስ ለቅስቀሳ ሥራ መጠቀም በመሆኑ የሕዝባዊ እምቢተኝነት አካል ነው። በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ውስጥ በርካታ የወረቀት ገንዘቦች በምሬት መግለጫነት ይውላሉ ተብሎ ይገመታል።

በተጓዳኝ በርካታ አማራጭ ስልቶች ሥራ ላይ መዋል ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፣ ተቀማጭ ገንዘብን ከህወሓት ባንኮች ማውጣት በቀላሉ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ስልት ነው። በውጋጋን ባንክ ተጀምሮ ወደ አንበሳ ኢንተርናሽናል ከዚያም ወደ ንግድ ባንክ ማሸጋገር ይቻላል።

በወገኖቻችን ላይ የግፍ ፍርድ የሚያስፈርዱ አቃቢያነ ህግ እና የግፍ ብይኖችን የሚሰጡ ዳኞች በቸልታ ሊታለፉ አይገባም። በእስር ቤቶችም በወገኖቻችን ላይ ሰቆቃ እየፈፀሙ ያሉ ጨካኞች ከሰላማዊ ሕዝብ ጋር ተደባልቀው ሰላማዊ ሕይወት እንዲመሩ ሊፈቀድላቸው አይገባም። እነዚህ ሁሉ ሊወገዙ፣ ሊገለሉ፣ በየደረሱበት ሊዋረዱ ይገባል።

በአገዛዙ መንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችን በሥራቸው ላይ መለገም ተቀባይነት ያለው በጎ ተግባር እንደሆነ ሰፊ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል። ከአምባገነን ሥርዓት ጋር መተባበር እኩይ ተግባር ሲሆን አምባገነን ሥርዓትን ከውስጥ መቦርቦር ደግሞ የሚበረታታ ሰናይ ሥራ ነው።

ለወያኔ አገዛዝ ግብር መክፈል የምናቆምበት ሰዓትም ተቃርቧል። በራሳችን ገንዘብ ገዳዮቻችን እንዲሰለጥኑብን መፍቀድ የለብንም። ስለሆነም "ግብር አንከፍልም"፤ "መዋጮዎቻችሁ አይመለከቱንም" የምንልበት ቀን ቀርቧል።

በፋይዳ የለሽ ምርጫ የሀገር ሀብት ሲመዘበር ማየት አንሻም። በአግባቡ ለማይቆጠር ድምፃችን አንድም ደቂቃ የምናባክንበት ምክንያት የለምና ሁላችንም የምርጫ ካርዶቻችንን ቀዳደን ቁርጭራጮቹን በየመንገዱ ልንበትናቸው ይገባል።

እነዚህን እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው የሕዝባዊ እምቢተኝነት የመጀመሪያ ደረጃዎች። እነዚህን እያደረግን በምስጢር መደራጀታችንን እንቀጥል። ከጥቂት በኋላ አምባገነኑን ሥርዓት የሚያንበረክክ ኃይል እንፈጥራለን። ጥቃት ቢደርስ የሚመክት ኃይል የተደራጀ በመሆኑም ሕዝባዊ እምቢተኝነትና ሕዝባዊ አመጽ ተቀናጅተው እንዲሄዱ ይደረጋል።

አርበኞች ግንቦት 7፡ የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሕዝባዊ እምቢተኝነትንና ሕዝባዊ አመጽን አቀናጅቶ ለመምራት የተዘጋጀ፤ ለዚህ የሚያበቃው ድርጅታዊ አቅም እየገነባ ያለ ድርጅት ነው። አርበኞች ግንቦት 7 "እንሰባሰብ በወያኔ ላይ የምናቀርባቸው ተቃውሞዎች በሙሉ ወደ እምቢተኝነት ከፍ እናድርጋቸው" ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ! ! !**

## የግዲቾ ብሄረሰብ አባላት ያነሱትን ተቃውሞ ተከትሎ ፖሊሶች አንድ ሰው ገድለው 8 አቆሰሉ

የግዲቾ ብሄረሰብ አባላት ተቃውሞውን ያስነሱት መሬታቸው ለትምባሆ ተክል እርሻ ለአንድ ባለሀብት መሰጠቱን ተከትሎ ነው። በደቡብ ክልል በጋሞጎፋ ዞን በምእራብ አባያ ወረዳ የሚኖሩት ቁጥራቸው እስከ 5 ሺ የሚደርሱ የብሄረሰቡ አባላት፣ ቀደም ብሎ በአባያ ሃይቅ መካከል በሚገኘው ደሴት ይኖሩ ነበር። ደሴቱ በሃይቁ ሙሉ በሙሉ መሸፈኑን ተከትሎ የብሄረሰቡ አባላት ሃንቲ ወደ ሚባል አጎራባች ቀበሌ በመሄድ ኑሮአቸውን ሲገፉ ቆይተዋል። ይሁን እንጅ የዞኑ ምክር ቤት የእርሻ መሬታቸውን ለ4 ኢንቨስተሮች በመስጠቱ፣ ነዋሪዎቹ በእርሻ መሬት እጦት ሲሰቃዩ ቆይተዋል። ባለፉት ጥቂት ወራት ደግሞ የብሄረሰቡን አባላት ሙሉ በሙሉ በሚያፈናቅልና መድረሻ በሚያሳጣ ሁኔታ ፣ መሬታቸው ለአንድ ትምባሆ አምራች ኢንቨስተር ተሰጥቷል። ነዋሪዎቹ በተወካይ ሽማግሌዎች አማካኝነት አቤቱታቸውን ለዞኑና ለክልል ምክር ቤት አባላት ሲያቀርቡ ቢቆዩም፣ በየደረጃው ካሉ ባለስልጣናት ያገኙት መልስ ግን ስድብ ብቻ ነው።

ባለፈው ማክሰኞ አዲሱ ባለሃብት ወደ አካባቢው በመሄድ ደኖችን መመንጠር ሲጀምር በአካባቢው የነበሩት ሴቶችና ህጻናት በመጮህ ተቃውመዋል። የአካባቢው ፖሊሶች ፈጥነው በመድረስ በጩኸት ሲቃወሙ ከነበሩት መካከል አንዷን አሮጊት ክፉኛ መደብደባቸውን፣ ጩኸቱን ሰምተው የተሰባሰቡት ወንዶችም ተቃውሞአቸውን መግለጻቸውን የአይን እማኞች ገልጸዋል። ፖሊሶች ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ያገኙትን ሁሉ ከመደብደብ አልፈው ጥይቶችን በመተኮስ አንዱን የብሄረሰቡ አባል በ4 ጥይቶች አናቱን መትተው ሲበታትኑት፣ 8ቱን ደግሞ ክፉኛ አቁሰለዋቸዋል። አንደኛው ሰው አንጀቱ አካባቢ ተመትቶ የህክምና እርዳታ እያገኘ ቢሆንም፣ ላይተርፍ ይችላል ተብሎአል። ሌሎች ደግሞ እጅና እግራቸው መሰባበሩን የአይን እማኞች ለኢሳት ተናግረዋል። "በጣም የሚያሳዝነው" ይላሉ ነዋሪዎች፣ "ሟቹ ለ6 ሰአታት ያክል መንገድ ላይ ወድቆ አስከሬኑ እንዳይነሳ መደረጉ ነው"። የብሄረሰቡ አባላት በከፍተኛ ድህነት ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ መሬታቸው በጉልበት ለባላሀብቱ ከተሰጠ፣ ወደ ከተሞች ተሰደው የጎዳና ተዳዳሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይናገራሉ። በጉዳዩ ዙሪያ የጋሞጎፋ ዞን ፖሊስ ጽ/ቤትን ለማነጋገር ያደረግነው ሙከራ ሳይሳካ ቀርቷል።

## አዲስ አበባ ኮልፌ ቀራንዮ ዉስጥ ክፍለ ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ድርጅታዊ ስራቸውን ከመስራት ይልቅ የግል ጥቅማቸውን በማሳደድ ስራ ላይ ተጠምደው እንደሚገኙ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ለፋሽስታዊው አገዛዝ ከፍተኛ ስጋት የሆነው ግን በሁለቱ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ በርካታ ሹማምንት ከሕዝብ ጎን እየተሰለፉና የነፃነት ትግሉን እየደገፉ መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎች በመገኘታቸው እንደሆነ ለማወቅ ችለናል።

## ልዩነታችን ጌጣችን፤ አንድነታችን ህልውናችን ነው

ኢትዮጵያ ስንል ብዙ የተለያዩ ዘውጎች፤ ብዙ የተለያዩ ቋነወቋዎችና ሀይማኖቶች በአንድነት ይዛና አስተሳስራ ብዙ ፈተ ናዎችን በማለፍ ለረጅም ዘመናት ህልውናዋን ጠብቃ የቆየች ሀገር መሆንዋ መታወቂያዋ ሀገር ማለት ነው። እንዳ ሳለ ፈችው ረጅም ዘመናት ሁሉ እንደየዘመኑ በህልውናዋ ላይ ይቃጣ የነበረውን ጥቃት እነዚያ በዘውጎች፤ በቋነወቋዎችና ሀይ ማኖቶች የተንቆጠቆጡት ልጆችዋ በአንድነት በመሰለፍ ብሎም ድል በመምታት ህልውናዋን አስጠብቀው መዝለቃቸው የነጻነት ሀገር የመሆን መለያዋ ምክንያቶች መሆናቸውንም የሚያሳይ ነው።

ይህ ልዩነታችንን ጌጡ አድርጎ ያስተሳሰረን ኢትዮጵያዊነት በነፃነት የዘለቀ ህዝብ ከማድረግ አልፎ በአንድ ወቅት የስልጣኔ ምንጭና የአለማችን ሀያል ህዝብ ከመሆን ጫፍ አድርሶን እንደነበር አይዘነጋም። በዚያው ልክ ይህ በልዩነታችን ላይ የተገነባ አንድነታችን ሲላላ ህልውናችን ከገደል አፋፍ ላይ የደረሰበት ዘመንም በታሪካችን ውስጥ መታየቱ አልቀረም። “ዘመነ-መሳፍንት” በመባል የሚታወቀው ጥቁር የታሪካችን ክፍል አንዱ ተጠቃሽ ሲሆን ሌላው ዛሬ የምንገኝበት የወያኔ ዘረኛ ዘመን ነው። ትናንት በዘመነ መሳፍንት ህልውናችን አደጋ ላይ ወድቆ ነበር፤ ዛሬም በወያኔ ዘረኞች ዘመን ህልውናችን ከከፋ አደጋ ላይ እንዲገኝ ተደርጓል። በአጭሩ ልዩነታችን ጌጣችን አንድነታችን ደግሞ የህልውናችን ማስጠበቂያ ዋነኛው ቁልፍ መሆኑን መገንዘብ ለማናም አያዳግትም።

ሌላው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በታሪካችን ዛሬ ለሁለተኛ ጊዜ በህልውናችው ላይ የከፋ አደጋ ያንዣበበት ወቅት ላይ መገኘታቸው ከማንም የተሰወረ አይደለም። ዘመነ መሳፍንት ትናንት ቋንቋ ዘውግና ሀይማኖት ሳይለይ በእያንዳዱ ኢትዮጵያዊ ህይወት ላይ አስከትሎት የነበረውን ችግርና በሀገሪቱም ከአዘቅት የከተተ ከመሆኑም በላይ ይኸው እስከዛሬ ድረስ ውደ ቀድሞ ታላቅነቷ ለመመለስ ከባድ መሰናክል ተክሎ ማለፉን ከትናንት ታሪካችን መረዳት እየተቻለ ዛሬ በእኛ ዘመን ዳግም ከትናንቱ የከፋ ጥልቅ አዘቅት ውስጥእንድንፈቅ በዘረኞች እየተገፋን መሆኑንና ሊያስከትል የሚችለውንም ውጤት ለመረዳት የተለየ እውቀት አይፈልግም። ዛሬ ይህ ልዩነትን እያጎሉና ቂም በቀልን እየዘሩ መጓዛ የጥቂቶች ፍላጎት መሆኑ ባይካድም ከዚህ ቀደም ያስከተለውንና ዛሬም እየታየ ያለውን አደጋ ተገንዝቦ ከወዲሁ መከላከል የእያንዳዳችን ሀላፊነት ሊሆን ይገባል።

ጥቂቶች የህዝብ አሳቢ በመምሰል የሚረጩት የልዩነት መርዝ በሌሎች ሀገራት ላይ ያስከተለውን ፈተናም እንዲሁ ቆ ም ብሎ መፈተሽና ውጤቱንም መመዘን የፈሰሰ ውሀን አፋሽ ከመሆን ማዳኑን መጠራጠር የለብንም። የሶቭየት ህብረት መ ፍረስ፤ የዩጎዝላቪያ እርስ በርስ መባላት፤ የሶማልያ መቋጫ ያጣ ትርምስ ....... ወዘተ ንፁሀንን በገፍ የበላና ዜጎችን ለኢኮኖሚ ድ ቀት የዳረገ፤ በገፍ ስደትን ያስከተለ፤ የጦርነቶቹ መዘዝ ከልጅ ልጅ የማይታረቅ ቂም እያስቋጠረ መገኘቱ ሲታይ ዛሬ በእ ኛም ሀገር ጥቂት የመገንጠል አባዜ የተጠናወታቸው ይዘውን ሊጓዙ የሚፈልጉበትን መንገድ የት ሊያደርሰን እንደሚችል ከራ ሳችንም ያለፈ ታሪክ ሆነ በአለማችን ላይ የታዩ ክስተቶች ውጤት የሆነውን ትርምስና ሽብር በመመልከት ልንማርበትና ከወዲሁ አንድነታችንን በማጠናከር ለመከላከል መስራት ግድ ይለናል።

ከላይ እንደ ምሳሌ የተጠቀሱት ሀገራት በመበታተን ያተረፉተረ ሽብረ፤ ጦርነት፤ ስደትና ድህነት መሆኑ የታዘብነው የዘመናችን ክስተት ሲሆን ቀደም ሲል ለሁለት ተከፍላ የነበረችው ጀርመን ዳግም ከሁለትነት ወደ አንድነት መምጣቷዋ በሰጣት ሁለንተናዊ ጥንካሬ የዓለምችን ታላላቅና ሀብታም ሀገራት በኢኮኖሚ ውድቀት ሲመቱ ያለአንዳች ጭግር የፈተናውን ወቅት ያለፈች ሀገር ለመሆን መብቃትዋን ከአንድነት ሊገኝ የሚችለውን ሁለንተናዊ ጥንካሬ አጉልቶ የሚያሳይ ነው። ሌላው ከሀ ገራችን ህልውናን የማስጠበቅ ፍልሚያ ታሪኮች ውስጥ ጎላ ብሎ የሚታየው የአድዋ ጦርነትና ድል የአንድነትን ዋጋ ከፍ አድርጎ የሚያሳይ አኩሪ ታሪክ ነው።

በዘመናዊ የጦር መሳሪያ ተማምኖ የመጣውን ወራሪ የኢጣልያ ጦር በተመጣጣኝ የጦር መሳሪበ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ተማምኖ የመጣውን ወራሪ የኢጣልያ ጦር በተመጣጣኝ የጦር መሳሪያና የሰለጠነ ሰራዊት ሳይሆ ን ቋንቋ፤ ዘውግና ሀይማኖት ሳይለያቸው ሁሉም በአንድነት ለሀገራቸው ህልውናና ለነፃነታቸው በአንድነት በመቆማቸው የተ ገኘ ድል መሆኑም መዘንጋት የለበትም።

ኢትዮጵያችን ደሀ ናት? አዎ ደሀ ናት። ህዝቧም ለዘመናት አንባገነን ስርአቶች እየተፈራረቁበት ህይወቱ የስቃይና የመከራ ሆኖ ቆይቷል? አዎ ቆይቷል። ሀገራችንን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት፤ ህዝቧንም ከስቃይና ከመከራ ህይወት አውጥቶ የተሻለ ሀገር፤ ለመፍጠር ዛሬ የወያኔ ዘረኛ ቡድን የሚያራምደው የመንደር ፖለቲካ እውን መፈትሄ ነውን? ብለን ስንጠይቅ ያለፉት 23 የወያኔ የስልጣን ዘመናት እውነቱን ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ። በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ህዝብ በጅምላ ስደት፤ ለቁጥር በሚታክት ሁኔታከመኖሪያ ቀዬ መፈናቀል፤ እስር ቤት በእስር ቤተረ መገንባት፤ እናትና ልጅ ተፈራርተው መመካከር ያልቻሉበት ዘመን፤ ድህነት ከሚባለው ደረጃ ተወርዶ ጭራሽ የሆቴል ትርፍራፊ በጉርሻ የሚሸጥበት ዘግናኝ ወቅት ላይ ለመገኘት ምክኒያት ከመሆኑም በላይ ሀገር አለኝ ብሎ መኩራት እንኳ ከማይቻልበት ህልውናችን ከከፋ አደጋ ላይ የሚገኝበት ወቅት ሆኖ እናገኘዋለን።

ዜጎችን ነቋንቋ በዘውግና በሀይማኖት ከፋፍሎ ለመግዛት የሚያራምደው በታኝ የጥፋት ፖለቲካ ሌላው ቢቀር ዛሬ በቀን ሶስት ጊዜ በልቶ የማደር ሰዋዊ መብት እንኳ ማስከበር ከማይቻልበት ሁኔታ ላይ መደረሱ ከእያንዳዱ ኢትዮጵያዊ የተሰወረ አይደለም። በአንባገነኖች የተጫነበትን የአገዛዝ ቀንበር አስወግዶ የነፃነት አየር የሚተነፈስበት፤ ፍትህ የሰፈነበትና መብቶች የተከበሩበት ሀገር ለመፍጠር በተከፈለ የህዝብ ልጆች የህይወት ዋጋ ለስልጣን የበቃው ወያኔ በማር በተለወሰ መርዘኛ የዘር ፖለቲካው ሳቢያ የተገኘው ውጤት የእለት ጉርስን እስከማጣት የደረሰ ሆኗል ማለት ነው።

በአጭሩ ዛሬ ከ23 አመታት በኋላ እንደ ትናንቱ ሁሉ ይህን ርእሰ-ጉዳይ ማንሳታችን ያለ ምክንያት አይደለም። ይህ በለዩነታችን መካከል ለመገንባት ደፋ ቀና የሚባልለት የልዩነት አጥር እስካሁን የተፈለገውን ያህል ባይሳካም በጠንካራው አንድነታችን ላይ ያጠላው ጥላ ለምን አይነት አሰቃቂ ህይወት የዳረገን መሆኑና ጥያቄዎቻችን ለሆኑት ፍትህ፤ እኩልነትና ነፃነት ምላሽ ከማስገኘት ይልቅ ይባስ ለከፋ አፈናና አገዛዝ የዳረገን መሆኑን ተገንዝበን ቀኑ ሳይመሽ ከወዲሁ ለመፍትሄው በጋራ መስራትብቸኛ አማራጭ መሆኑን ሁሉም እንዲገነዘበው ነው።

3000 ዘመን ያለ ፈተና የተቆጠረ የነፃነት ዘመን አይደለም። የገጠሙን ፈተናዎች በሙሉ በልዩነቶቻችን ላይ በተገነባው ጠንካራ ኢትዮጵያዊ አንድነታችን ተጠብቆ የተገኘ እንጂ...... ዛሬም ቢሆን ዜጎች ልዩነቶቻቸውን የጥንካሬያቸው መሰረት በማድረግ በአንድነት ነፃነታቸው የተረጋገጠበት፤ መብቶቻቸው የተከበሩበት፤ ፍትህ የሰፈነበት ሀገር ለመፍጠር የተጀመረውን ሁለገብ ትግል በማጀብ ከዳር ለማድረስ ለመነሳት ያለፉት 23 አመታት ከበቂ በላይ መሆኑን አጢነን በቃ የምንልበት ወቅት ላይ እንደምንገኝ ለማሳሰብ ነው።

ትናንትም ዛሬም ነገም ልዩነቶቻችን ጌጣችን አንድነታችን ህልውናችን መሆናቸውን ተረድተን ሳይመሽ ሁላችንንም በእኩልነት የማታስተናግድ የሁላችንን ኢትዮጵያ ለመገንባት እንነሳ!!!!!

**ኢትዮጵያችን ለዘላለም ትኑር!!!!**

---

## ወያኔና ቻይና የዲፕሎማቲክና የሰርቪስ ፓስፖርት የያዙ ዜጎቻቸዉ ያለቪዛ መመላለስ እንዲችሉ ለማድርግ ተስማሙ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝና አጋሩ የቻይና አጋዛዝ የሁለቱ አገር ዜጎች የዲፕሎማቲክና የሰርቪስ ፓስፖርት እስከያዙ ድረስ ያለ ቪዛ መንቀሳቀስ የሚያስችል ስምነት ሊፈርሙ መባሉ ከወደ አዲስ አበባ ተሰማ። በስምምነቱ መሠረት የዲፕሎማትና ሰርቪስ ፓስፖርት የያዙ የሁለቱ ሀገራት ሰዎች ለ30 ቀናትና እንደአስፈላጊነቱ ሊራዘም የሚችል ቆይታ ያለቪዛ እንዲገቡ ይፈቅዳል። ይህን ቪዛን የሚያስቀረው ስምምነት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት የሁለቱ ሀገራት ዜጎች ለስራ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እየጨመረ በመምጣቱ ነው ተብሎአል። በሁለቱ ሀገራት ስምምነት መሰረት ከምክትል ሚኒስትር በላይ የሆነ ማእረግ ያላቸው የማእከላዊ መንግስቱ ባለስልጣናትና አፊሰሮች ወይንም ከሜጀር ጄኔራል በላይ የሆነ ማእረግ ያላቸው የመከላከያ ባለስልጣናት ለኦፊሴላዊ ጉብኝት ሲንቀሳቀሱ ያለቪዛ የመግባት መብታቸውን ያስከብራል። የዲፕሎማቲክ ወይም የሰርቪስ ፓስፖርት የያዙ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን አባላትና ቤተሰቦቻቸው የሌላኛውን ተዋዋይ ወገን ሁሉንም ሕጋዊ ውክልና መስፈርቶች ካሟሉ ፣ ተቀባይ ሀገር በደረሱ በ30 ቀናት ውስጥ ቪዛ ማግኘት ሳይጠበቅባቸው እስከ ውክልናቸው ጊዜያቸው መጨረሻ ድረስ ያለቪዛ ወደሀገር መግባትና መውጣት እንደሚችሉ በስምምነቱ ላይ ተቀምጧል።

ይህ ስምምነት በቻይና ዩኒቨርሲቲዎችና የጦር አካዳሚዎች ውስጥ ከፍተኛ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ የከፍተኛ ባለለስልጣናት ልጆችና ቤተሰቦች እንዲሁም ከከፍተኛ በለስልጣናት ጋር ተቀናጅተው የቻይና ምርቶችን በሚስጢር ለሚነግዱና ለሚያስነግዱ የሥርዓቱ ሰዎች የተሻለ ምቾትን ለመስጠት ታልሞ የተደረገ ስምምነት ሊሆን እንደሚችል ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ጠቁመዋል። ስምምነቱ ፓርላማው ሰሞኑን ያጸድቀዋል ተብሎ ይገመታል።

## የብር ተቃውሞው እንደቀጠለ ነው

የኢትዮጵያ ህዝብ ከዘረኛዉ ወያኔ የግፍ፤ የዘረኝነትና የስቃይ አገዛዝ ለመላቀቅ የሚየደርገዉን ተቃዉሞ በመቀጠል ከአሞኑ አንድ ከዚህ ቀደም ተደርጎ የማያዉቅ የህዝባዊ ተቃዉሞ በየቦታዉ በመታየት ላይ መሆኑን ጉዳዩን የተከታተሉ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ይህ በአይነቱ አዲስ የሆነዉ ህዝባዊ ተቃዉሞ በአገሪቱ የመገበያያ ገንዝብ በብር ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ስርአት እንዲያመጣ፣ ህዝቡ ለመብቱ እንዲነሳ የሚጠይቁ ጽሁፎች በተለያዩ የብር ኖቶች ላይ ተጽፎ በመታየት ላይ ነዉ። ዜጎች በተለያዩ የብር ኖቶች ላይ " ህዝባዊ እምቢተኝነት ይቀጥላል፣ ፍትህ እኩልነት፣ ነጻነት፣ ከዘረኝነት የጸዳች አንዲት ኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ድምጽ ይሰማ፣ ፍትህ፣ ዘረኝነት ይብቃ፣ ጭቆና ይብቃ የሚሉና ሌሎችም መፍክሮች ተጽፎባቸው እየተሰራጩ ነው። የወያኔ አገዛዝ እንደለመመደዉ ተቃዉሞዉን በአፈና፤ በድብደባና በእስር ለመግታት ቢሞክርም ለግዜዉ ብዛት ያላቸዉና የተቃዉሞ መልዕክቶችን የያዙ የብር ኖቶች ገበያዉን መዉረራቸዉን ለማወቅ ተችሏል።

## የአዲስ አበባ ከንቲባ የከተማዋን የጸጥታ ጉዳይ ለኦሮምያ ምክር ቤትም ሪፖርት እንዲያቀርቡ ታዘዙ

የአዲስ አበባንና የኦሮምያን የጸጥታ ሁኔታ ለማስተሳሰር፣ የኦሮምያን ልዩ ሃይልና የፌደራል ፖሊሶችን በጋራ በአዲስ አበባ ለመጠቀም ሲባል፣ መስተዳድሩ የጸጥታ ጉዳዮችን ለጨፌ ኦሮምያም ጭምር ሪፖርት እንዲያደርግ ታዟል።

የእቅዱ ዋና ነዳፊ የሆኑት የጠ/ሚኒስትሩ አማካሪ አባይ ጸሃየ፣ ጸጥታን በተመለከተ የኦሮምያ ምክር ቤት ሪፖርት እንዲቀርብለት፣ የልማት ጉዳዮችን በተለይ መሬትን በተመለከተ ደግሞ የአዲስ አበባ ምክር ቤት ሪፖርት እንዲቀርብለት አዘዋል። ምርጫው ተጠናቆ አዲስ ምክር ቤት እስከሚመሰረት ድረስ በዚህ መንገድ እንዲቀጥል አባይ ጸሃየ ቢያዝዙም፣ ከንቲባ ድሪባ ኩማ ሳይቀበሉት ቀርተዋል። ትእዛዙ ወደ ምክትል ከንቲባው አባተ ስጦታው እንዲወርድ ቢደረገም፣ አቶ አባተ ኦሮምኛ አይችሉም በሚል አቶ ድሪባ በግድ እንዲቀበሉት ተደርጓል።

ከንቲባ ድሪባ ጨፌ ኦሮምያ ተገኝተው ሪፖርት የቃረቡ ቢሆንም፣ ከምክር ቤት አባላት የተነሱትን ጥያቄዎች መመለስ ሳይችሉ ቀርተዋል። ከንቲባ ድሪባ " የአዲስ አበባ የጸጥታ ጉዳይ ለምርጫው ሲባል በኦሮምያ ምክር ቤት እንዲደመጥ ተወስኗል" ብለዋል።በአዲሱ አሰራር የኦሮምያ ክልል ምን እንደሚያገኙ የጠየቁት የምክር ቤት አባላት በቂ ምላሽ አላገኙም። ይሁን እንጅ አሁንም መሬት ለማስፋት፣ የኦሮምያና የአዲስ አበባ ክልሎችን በማጣረስና ውሳኔዎችን በመደራራብ ችግር ለመፍጠር ታስቦ የተካሄ እንዳይሆን ፣ አካሄዱም ኢህአዴግን ለከፋ ችግር ሊዳርገው እንደሚችል ተናግረዋል።

## እንግሊዝ ከሰብአዊ መብቶች ጋር በተያያዘ ለወያኔ የምትሰጠውን እርዳታ ማቋረጡዋን አስታወቀች

ብሉምበርግ የእንግሊዝ ባለስልጣናትን ጠቅሶ እንደዘገበው እንግሊዝ በኢትዮጵያ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለመደጎም ትሰጥ የነበረውን እርዳታ ያቋረጠችው፣ መንግስት መጪውን ምርጫ ተከትሎ ጋዜጠኞችንና የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎችን ማሰሩንና መዋካቡን በመቀጠሉ ነው።የእንግሊዝ አለማቀፍ የልማት ተራድኦ ጸሃፊ ጀስቲን ግሪኒንግ፣ እንግሊዝ አጠቃላይ የሆነ የኢኮኖሚ ድጋፍ ለማድረግ መወሰኑዋን ተከትሎ፣ ቀድም ብሎ ይሰጥ የነበረው የማህበራዊ አግልግሎት ድጋፍ እንደተቋረጠ ለእንግሊዝ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ቀርበው አስረድተዋል።

ባለስልጣኑ በኢትዮጵያ የሚፈጸመው የሰብአዊ ና የፖለቲካ ነጻነቶች ገፈፋ አሳሳቢ መሆኑ እርዳታው እንዲቋረጥ አድርጎታል። በተለይም ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ ነጻ ምርጫ የማካሄድና የጸጥታ ሃይሎችን ተጠያቂ የማድረጉ ነገር አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ ለተወሰደው እርምጃ ምክንያት መሆኑን ባለስልጣኑ ለፍርድ ቤቱ ተናግረዋል።የእንግሊዝ ተራድኦ ድርጅት በዚህ አመት 368 ሚሊዮን ፓውንድ ወይም በኢትዮጵያ ብር 11 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ለመስጠት አቅዳ ነበር፤ ባለፉት አምስት አመታት ከ700 ሚሊዮን ፓውንድ ያላነሰ ገንዘብ ደግፋለች።ዘገባው እንደሚለው አስቀድሞ የተመደበው ገንዘብ የህዝብ መረታዊ አግልግሎቶችን ከመደጎም ይልቅ ሌሎች የጤና፣ የትምህርትና የውሃ ስራዎችን ለማገዝ ይውላል። እንዲህ አይነቱ ድጋፍ የእንግሊዝ መንግስትን ከተጠያቂነት የሚያድነው ሲሆን፣ የኢትዮጵያ መንግስትም የተለየ ሃላፊነት እንዲወጣ አያስገድደውም ብሏል።

በሌላ ዜና ደግሞ በደቡብ ኦሞ የሚካሄደው የስኳር ፋብሪካ ግንባታ በአካባቢው የጸጥታ መደፍረስ ሊያስከትል ይችላል በሚል ለጋሽ አገራት ስጋታቸውን ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን ከቻይና የልማት ባንክ በተገኘ ብድር 6 የስኳር ፋብሪካዎችን ለመገንባትና 150 ሺ ሄክታር መሬት የሚሸፍን የሸንኮራ ገዳ ተክል ለማካሄድ ማቀዱን የሚገልጹት ለጋሽ አገራት፣ ፕሮጀክቱ በአካባቢው በባህላዊ መንገድ በከብት እርባታ ኑሮአቸውን የሚገፉትን ማህበረሰቦች ህይወት ከማወኩም በላይ ለግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል።

በመቶሺዎች የሚቆጠሩ የፋብሪካ ሰራተኞች ወደ አካባቢው በሚጓዙበት ወቅት ፣ የብሄር ግጭቶችን ሊያባብስ ይችላል በሚል ለጋሾቹ ስጋታቸውን ገልጸዋል። 27 አገራት በጋራ በመሆን ባወጡት መግለጫ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚደረገው እሩጫ፣ በተለይም የቦዲና የሙርሲ ማህበረሰቦችን ህይወት የሚያውክ በመሆኑ፤ በአካባቢው ብጥብጥና አለመረጋጋት ሊያስከትል ይችላል ሲሉ አስጠንቅቀዋል። የአካባቢው ነዋሪዎች የኦሞ ወንዝ ፍሰት በሚገነባው የግልገል ግቤ 3 የሃይል ማመንጫ ግድብ አማካኝነት የሚቀንስ ከሆነ የግጦሽና ለም የሆኑ ቦታዎችን እንደሚያጡ ስጋታቸውን ገልጸዋል። መንግስት ስለሚገነቡት የስኳር ፋብሪካዎች ግልጽ መረጃ እንዲሰጥ፣ የአካባቢውን ህዝብ ፍላጎት በጽሞና እንዲያዳምጥ፣ ግጭትን ለማስወገድ ሲባል ለግንባታው የሚያደርገውን እሩጫ እንዲገታ 27ቱ ለጋሽ አገራት ጠይቀዋል።

## በረከት ስምኦን ራሱን ከምርጫ ክርክር አገለሉ

በአለማቀፍ ታዛቢዎችና በኢትዮጵያውያን በቂ ትኩረት ያልተሰጠውን የግንቦት 16 ቀን 2007 ምርጫ ክርክር የሚሳተፉለትን መሪዎች ሲያፈላልግ የነበረው ኢህአዴግ፣ ለመጀመሪያው ዙር የክርክር መድረክ የሚሆኑትን ሰዎች ሲመርጥ፣ በረከት ስምኦን እራሱን አግልሏል።ኢህአዴግ 23 አመራሮችን ለክርክር በእቅድ የያዘ ቢሆንም፣ ከእነዚህ ወስጥ በመጀመሪያው ዙር ማጣሪያውን ያለፉት ሬዲዋን ሁሴንና ደሰታ አስፋው ብቻ ሲሆኑ ሌሎቹ 21 አመራሮች ቀጥተኛ ተፎካካሪ መሆን አይችሉም ተብለዋል። በሁለተኛው ዙር ማጣራት ደግሞ አባይ ፀሃየ ፣ካሳ ተክለብርሃን ፤ ተፈራ ደርበውና ሽመልስ ከማል እንዲያልፉ ተደርጓል። ኢህአዴግ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ማህደር ሲያጠና ከርሞ ዛሬ በዝግ ለተከራካሪ አመራሮች ገለጻ እያደረገ ነው።

በመጀመሪያው ዙር በእጩነት ቀርበው አይመጥኑም ወይም ኢህአዴግን ያዋርዱታል ከተባሉት ውስጥ አባ ዱላ ገመዳ፣ አስቴር ማሞ፣ ዘነቡ ታደሰ፣ ሙፈሪያት ከማል፣ ከበደ ጫኔ፣ ወልዱ ይምሰል፣ አህመድ አብተው፣ ተመስገን ጥላሁን፣ አሊ ሲራጅ፣ ታደሰ ሃይሌ፣ ፍሬህይወት አያሌውና ብስራት ጋሻው ይገኙበታል።

በረከት ስምኦን በክርክር መድረኮች ላይ እንዲገኝ ቢጠየቅም አልፈልግም በሚል እራሱን ማግለሉ ታወቋል፤ ሆኖም በምን ምክንያት እራሱን እንዳገለለ ከበረከት ስምኦን ከራሱም ሆነ ከፓርቲዉ የተሰጠ ማብራሪያ የለም። ከመጋቢት 04 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በሚካሄደው የፓርቲዎች ክርክር ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግን ጨምሮ በአንድ የክርክር መድረክ ላይ አምስት ፓርቲዎች የሚሳተፉ ሲሆን በአጠቃላይ ዘጠኝ መድረኮች ይካሄዳሉ። ፓርቲዎቹ በተመረጡት አጀንዳዎች ላይ ያላቸውን አቋም በሚገባ ለማንጸባረቅ በአንድ የክርክር መድረክ የሚሳተፉት ፓርቲዎች ብዛት አምስት እንዲሆን ተደርጓል። በክርክሩ ላይ ተቃዋሚዎች እያንዳንዳቸው አንድ ተከራካሪ እና አንድ አማካሪ እንዲሁም ገዢው ኢህአዴግ ሁለት ተከራካሪና አንድ አማካሪ በመያዝ ይከራከራሉ። የዘንድሮውን ምርጫ የአውሮፓ ህብረት አይታዘበውም። ህብረቱ በምርጫው መሳተፍ ዋጋ የለውም በሚል ምክንያት መሆኑን በቅርቡ በህብረቱ ውስጥ በተዘጋጀ አንድ ዝግጅት ላይ ተገልጿል።

## ዋሽንግተን ዲሲ ዉስጥ ከፍተኛ ተቃዉሞ የደረሰበት የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት የብልግና ምላሽ ሰጡ

የሱማሌ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ አብዲ መህመድ ኡመር በዋሽንግተን ዲሲ ከፍተኛ ተቃውሞ አጋጠማቸው።

ፕሬዚዳንቱ በተገኙበት ሆቴል የተገኙ ኢትዮጲያውያን "ሰውዬው እጃቸው በደም የተጨማለቀ፣ የሱማሌ ክልል ወጣቶችን በመግደል በዘር ማጥፋት ክስ የተመሰረተባቸውና እና ለዚህም በዓለማቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ሊጠየቁ የሚገባ ወንጀለኛ መሆናቸውን በማውሳት ከፍ ያለ ተቃውሞ አሰምተዋል። በደረሰባቸው ድንገተኛ ተቃውሞ የተበሳጩ የመሰሉት የክልሉ ፕሬዚዳንት አቶ አብዲ መህመድ በተደጋጋሚ ጸያፍ ቃል ሲናገሩ ተደምጠዋል። ስለ ሁኔታው መረጃ ደርሰሠቸው በስፍራው የደረሱ የአሜሪካ የፀጥታ ሰራተኞችም ተቃውሞውን አብረደውታል።

### የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ከፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## የዴምህት አባላት ናቸው የተባሉ ሁለት የመቀሌ ነዋሪዎች ላይ የሽብርተኝነት ክስ ተመሰረተ

የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ አባላትን ሲመለምሉና መንግሥትንና ተቋማቱን ሲሰልሉ ተደርሶባቸዋል፣ ደግሞም የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ዴምሕት) ቡድን ምልምሎች ናቸው" ባላቸው ሁለት ተጠርጣሪዎች ላይ በዐቃቤ ህጉ አማካይነት ክስ መሠረተ።"የወንጀሉ ድርጊት በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ወይም የአይዲዎሎጂ ዓላማን ለማራመድ፣ ሕዝብን ለማስፈራራትና በመንግሥት ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ሲንቀሳቀሱ ነበር" ተብለው ክስ የተመሠረተባቸው፣ ነዋሪነታቸው በትግራይ ክልል መቐለ ከተማ የሆኑት አቶ አማረ ተወልደና አቶ ታሪኩ በላይ ላይ ናቸው።

የፌዴራል አቃቤ ህግ በክሱ "ተከሳሾቹ የሽብር ቡድን ነው ከተባለው ድርጅት ጋር በስልክ በመገናኘት፣ አባል በመሆንና መመርያ በመቀበል ኢትዮጵያ ውስጥ አባላትን በመመልመል፣ የኢትዮጵያ ተቋማትን በመሰለልና መረጃ አሳልፈው በመስጠት በሽብር ወንጀል ውስጥ የተሳተፉ ናቸው" ይላል።

አቃቤ ህግ አቶ አማረ ተወልደ በተባሉት አንደኛ ተከሳሽ ላይ ያቀረበው ዝርዝር ክስም "ኢትዮጵያ ውስጥ እያሉ ያውቋቸው ከነበሩትና አሁን ኤርትራ ከሚገኙት የትሕዴን ወይም ዴምሕት አመራር አቶ ጐይቶም በርሔ ጋር በተንቀሳቃሽ ስልክ እየተደዋወሉ የግለሰቦችን ተንቀሳቃሽ ስልክ ይሰጡ ነበር" ብሏል።

አቶ አማረን በሽብርተኝነት ያስከሰሳቸውና አቀበሉት የተባለው መረጃም፡- "የኢትዮጵያ መንግሥት -ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብሰባ እንዳይጠሩ ይፈልጋል፣ ሕዝቡ በስብሰባ እንዳይሳተፍ አፈና ያደርጋል የሚሉ" መሆናቸው በአቃቤ ህግ ክስ ተመልክቷል።

እንዲሁም በጭላ፣ በኢሮብና በማይጨው በሚገኙ የዓረና ትግራይ ለሉዓላዊነት ፓርቲ አባላት ላይ ችግር እያደረሰባቸው መሆኑን፣ ዓረና ፓርቲ ውቅሮ ከተማ ውስጥ የተሳካ ሕዝባዊ ስብሰባ ማድረጉን፣ አቶ ብርሃነና አቶ አብርሃ በተባሉ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ስብሰባው መመራቱን መረጃ ሲያስተላልፉ ነበር ያለው አቃቤ ህግ፤ "መንግሥት ያላደረገውን እንዳደረገና በሕዝብ ላይ በደል የደረሰ በማስመሰል ሐሰተኛ መረጃ አስተላልፈዋል ብሏል።

በትግራይ ሕዝብ ላይ የተለየ በደል እየደረሰ መሆኑን፣ በወልቃይት የስኳር ፋብሪካ ለመገንባት በሚል የአካባቢው ነዋሪዎች ያለምንም ካሳ እየተፈናቀሉ እንደሆኑ የሐሰት መረጃዎችን በማቀበል አገርን አደጋ ላይ የሚጥል እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል ያለው አቃቤ ህግ፤ "ሁለቱም ተከሳሾች ትሕዴን የሚባል ስያሜ ያለው የሽብር ቡድን ውስጥ አባል በመሆንና ከቡድኑ አመራሮች ጋር በስልክ መረጃ በማስተላለፍ፣ በፈጸሙት በሽብርተኛ ድርጅት ውስጥ ተከሰዋል" ብሏል።

በኢትዮጳያ የጸረ- ሽብር ህጉም ሆነ አዋጁ የፖለቲካ ተቀናቃኝን ማጥቂያ መሳሪያ እንደሆነ በዓለማቀፍ ደረጃ የታወቀ ቢሆንም፤ ደምሒት ለይስሙላም ቢሆን በፓርላማው በሽብርተኝነት ባልተፈረጀበት ሁናቴ አቃቤ ህግ ተከሳሹቹን "የሽብርተኛ ድርጅት አባል በመሆን" ብሎ መክሰሱ ታዳሚዎችን አስገርሚል።

ሌላው ታዳሚዎችን ያስገረመው በሽብር ተከሳዎቹን ያስከሰሳቸውና አስተላልፈውታል የተባለው መረጃ ይዘት በግልጽ የሚታወቅና ተቃዋሚዎችና ህብረተሰቡ በየጊዜው የሚናገሩት መሆኑ ነው ያለው ወኪላችን፤ "መንግስት ተቃዋሚዎች ህዝባዊ ስብሰባ እንዲያደርጉ አይፈቅድም" ብሎ ማውራት ሀገርን አደጋ ላይ በመጣልና በሽብር ወንጀል ማስከሰሱ፤ የሽብርተኝነት ህጉ ጥያቄ የሚያነሱ ዜጎችን መቅጫ ለመሆነ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው ብሏል።

## ጄ/ል ሳሞራ የኑስ በአየር ሃይል አባላት ላይ እየዛቱ መሆናቸው ተሰማ

አብራሪዎች ባለፉት 6 ወራት ከድሬዳዋ አየር ሃይል ግቢ ጠፍተው ተቃዋሚዎችን መቀላቀላቸውንና መሰደዳቸውን ተከትሎ ኢታማዦር ሹሙ ሳሞራ የኑስ በቀሪዎቹ ላይ የዛቻና የማስፈራሪያ ንግግሮችን በማድረግ ላይ መሆናቸው ተሰምቷል ።የአየር ሃይል ምንጮች እንደተናገሩት፡-ጀነራሉ "ከጠፉት የአየር ሃይል አባላት ጋር ግንኙነት ነበራቸው"ያሏቸውንና "ሊጠፉ ሲሉ ተያዙ የተባሉ ሌሎች የአየር ሃይል አባላትን" ለቀሪዎቹ አባላት ሲያሳዩ ሰንብተዋል። ኢታማዦር ሹሙ ሰሞኑንም እነኚህኑ "ከተቃዋሚዎች ጋር ግንኙነት አላቸው" ያሏቸውን አባላት፡- " የውስጥ ተቃዋሚዎች" ተያዙ በማለት በተለያዩ የአየር ሃይል ግቢዎች እያዞሩ በማሳየት ሌሎችን የአየር ሀይሉን አባላት ለማስፈራራት ሙከራ በማድረግ ላይ መጠመዳቸው ታውቋል።

እንደ ምንጮች ገለጻ፡- "ሊጠፉ ሲሉ ተያዙ" የተባሉ የተለያዩ የአየር ሃይል አባላት የእስረኛ ህጋዊ መብታቸው ተገፎ በሌሎች የአየር ሃይል አባላት ፊት ቀርበው እንዲሸማቀቁና ክብራቸው እንዲነካ መደረጉ፤ ብዙ የአየር ሃይል አባላትን አስቆጥቷል። እነዚሁ የአየር ሀይል ምንጮች፤አብራሪዎቹ እውነት ተቃዋሚዎች ናቸው ቢባል እንኳ ፍርድ ቤት መቅረብ ሲገባቸው፣ ታስረው ሰራዊቱ ፊት እንዲቀርቡ መደረጉ የአገዛዙን ባህሪ ያሳየነ ነው በማለት ለኢሳት ገልጸዋል። የአየር ሃይል አባላት አምነውበት ማገልገል ሲገባቸው በማስፈራራት በሰራዊቱ ውስጥ እንዲቆዩ ለማድረግ የሚደረገው መኩራ ቁጣንና ቅሬታን ከማባባስ ውጭ የሚፈይደው ነገር እንደሌለም እነዚሁ የአየር ሀይል አባላት ተናግረዋል።

ጄ/ል ሳሞራ ከዚያም አልፈው፡- "ኢሳት ኤርትራ ውስጥ ቃለ-መጠይቅ ያደረገላቸውን አብራሪዎችንና ቴክኒሻኖችን ይዘን እናመጣቸዋለን" እያሉ ሲዝቱ እንደነበር፤ በግምገማ ተወጥረው የሰነበቱት የአየር ሃይል አባላት ተናግረዋል። በአየር ሃይል አባላትና- በሰራዊቱ ከፍተኛ አዛዦች መካከል መተማመን መጥፋቱን የሚናገሩት እነኚሁ የአየር ሀይል ባልደረቦች፣ በዚህም ምክንያት ጄ/ል ሳሞራና ሌሎች አዛዦች ግራ እንደተጋቡ አክለዋል። በመጀመሪያ "ምን እናድርግላችሁ?" በሚል የማባበል ቃል መቀራረብ ለመፍጠር ቢሞክሩም ሰራዊቱ የሚያነሳው የመብት ጥያቄ በቀላሉ የሚመለስ ሆኖ ባለመገኘቱ ወደ ማስፈራራት መገባቱን የአየር ሃይል አባላቱ ይናገራሉ። ግምገማውን ተከትሎ ቀደም ብለው ከጠፉ የአየር ሃይል አባላት ጋር ግንኙነት ነበራቸው የተባሉ ቁጥራቸው ከ7 የማያንስ የአየር ሃይል አባላት መታሰራቸውን ምንጮች አክለው ገልጸዋል።

## ወደ አረብ ሀገራት በሕገወጥ መንገድ የሚደረገው ጉዞ እየጨመረ ነው

ወደ አረብ ሀገራት በሕጋዊ መንገድ የሚደረገው ጉዞ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ከአንድ ዓመት በፊት ከታገደ በሃላ ሕገወጥ ዝውውሩ በከፍተኛ ደረጃ ማደጉን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ጠቁመዋል። የሥራ ስምሪት ህጉ እስኪስተካከል ድረስ ለስድስት ወራት ብቻ ጉዞው እንዲታገድ መንግሥት ወስኖ የነበረ ቢሆንም፣ እገዳው ሳይነሳ ከአንድ ዓመት ከአራት ወራት በላይ አስቆጥሮአል። በዘርፉ የተሰማሩት ድርጅቶችም አብዛኛዎቹ ከእገዳው ጋር ተያይዞ ለቢሮ ኪራይና ለሰራተኞች ወጪ በማድረጋቸው ለኪሳራ በመዳረጋቸው ምክንያት ከሥራው ለመውጣት የተገደዱ ሲሆን፣ ይህ በመንግሥት የተፈጠረ ክፍተት ደግሞ በሕገወጥ መንገድ በድንበሮችና የጎረቤት ሀገራትን እንደመተላለፊያ በመጠቀም ሰዎችን ለሚያዘዋውሩ ሕገወጦች መልካም አጋጣሚ እንደፈጠረላቸው ታውቆአል።ሕገወጥ አዘዋዋሪዎቹ በአንድ ሰው ከ10 እስከ 40 ሺህ ብር በመቀበል ወደተለያዩ የአረብ ሀገራት በተለይ ኬንያንና ጅቡቲን መሸጋገሪያ በማድረግ ሴት የቤት ሠራተኞችን በማስወጣት ላይ መሆናቸው በኢትዮጵያዊኑ ላይ የሚደርሰውን እንግልት አባብሶታል።

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አሁን በስራ ላይ ያለውን አዋጅ በማሻሻል በውጪ ሀገር ስራ ስምሪት ረገድ የሚታዩ ችግሮችን እቀርፋለሁ ቢልም፣ ያቀደውን ማሳካት ባለመቻሉ በተቃራኒው ሕገወጥ ዝውውር እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ ማድረጉ እንዳሳዘናቸው ምንጮቹ ጠቁመዋል። የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ መ/ቤት ከሁለት ወራት በፊት ባወጣው የ2014 ሪፖርት ሕገወጥ ዝውውሩ መባባሱን በመጠቆም በርካታ ኢትዮጵያዊያን ወደመካከለኛ ምስራቅ ሀገራት ሲሰደዱ ጅቡቲ፣ ግብጽ፣ ሱዳን፣ እና የመንን እንደመሸጋገሪያ እንደሚጠቀሙ አስታውቆአል። በመካከለኛ ምስራቅ ሀገራት በቤት ሠራተኝነት የሚቀጠሩ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች አብዛኛዎቹ ለጉልበት ብዝበዛና ለወሲብ ባርነት ከመዳረጋቸውም በተጨማሪ ድብደባ፣ አልፎ አልፎም ግድያ ይፈጸምባቸዋል። የኢትዮጵያ መንግስት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት የተቀመጡትን ዝቅተኛ መስፈርቶች ማሟላት አልቻለም ሲል ስቴት ዲፓርትመንቱ በይፋ መውቀሱ ይታወቃል።